# መጽሐፍ ቅዱስ ለህፃናት

## አቅራቢዎች

# ተወዳጅ ልጅ ባሪያ ሆነ



ጸሐፊው: Edward Hughes
ምሣሌ አቅራቢው: Byron Unger; Lazarus
የተተረጎመው: Eyerusalem Dechasa
ያሻሽለው (አሻሽሎ የጻፈው): M. Kerr; Sarah S.

ታሪክ 7 ከ 60 ዎቹ መሃከል

www.M1914.org

***Bible for Children,*** *PO Box 3, Winnipeg, MB R3C 2G1 Canada*

ፈቃድ፡- ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ማባዛት ወይም ማተም ይቻላል
ነገር ግን ይህ መሆን የሚችለው ለሽያጭ ካላቀረባችሁ ብቻ ነው።

አማርኛ

Amharic

ይስሃቅ ልጁ ያዕቆብ ቤት ስለነበር በጣም ደስተኛ ነበር። ዔሳው እንኳን በአንድ ወቅት ለመግደል ምሎ የነበረውን ወንድም ተቀብሎታል። ነገር ግን የያዕቆብ ልጆች ደስታኛ አልነበሩም ምክንያቱም ታናሽ ወንድማቸው ዮሴፍ
በአባታቸው ተወዳጅ ነበርና።





የዮሴፍ ወንድሞች ሕልሙን ሲነግራቸው ይበልጥ ተበሳጩ። "የእኔ የእህል ነዶ ከፍ ብሎ ቆመ እናም የወንድሞቼ ነዶዎች ሰገዱለት" አላቸው። ይህ ሕልም ዮሴፍ ከወንድሞቹ የበለጠ አስፈላጊ ይሆናል ማለት ነው።




በዮሴፍ ሁለተኛ ሕልም ላይ ፀሐይ, ጨረቃና ከዋክብቶች ለእሱ ሰገዱለት። አባቱ ያዕቆብ እንኳ ራሱን ከወላጆቹና ከወንድሞቹ በላይ ስላደረገ ተበሳጨ።
3


አንድ ቀን ያዕቆብ ዮሴፍን ወንድሞቹ መንጎቻቸውን ወደሚጠብቁበት ወደ እርሻው ቦታ ላከው።
4


ወንድሞቹ ሲመጣ አዩት። "ህልመኛውን እንግደለው!" ብለው አጉረመረሙ። ዮሴፍ በእሱ ፊት ያለውን አደጋ አላውቅም ነበር።
5


ሮቤል ታላቅ ወንድሙ አልተስማማም። "ደም ማፍሰስ የለብንም" አለ። "ተመልከቱ, እዚህ ጉድጓድ አለ እዚህ እንዲሞት እንጣለው" ብሎ ሀሳብ አቀረበ። ሮቤል በሌሊት መጥቶ ዮሴፍን ለማዳን አቅዶ ነበር።
6


ዮሴፍ በደረሰ ጊዜ ወንድሞቹ ያዙትና ያዕቆብ ለተወዳጅ ልጁ የሰራለትን በቀለማት ያጌጠችውን ቀሚስ አወለቁበት። ከዚያም ወደ አስከፊው ጉድጓድ ውስጥ ጣሉት።
7


ሮቤልም ዝም ብሎ ነበር። ብዛት ያላቸው ግመሎች ወደ ግብፅ በመጓዝ ላይ ነበሩ። ይሁዳም ወንድሞቹን "ዮሴፍን እንሽጠው" በማለት ጮኸ። እነሱም ተስማሙና ዮሴፍን በሀያ ብር ብር ሸጡት።
8


ዮሴፍም የሚረዳው ሰው ሳይኖር ከቤተሰቦቹና ከትውልድ ሀገሩ ሲወስዱት ሲያይ እጅግ ፈራ።
9


"ይህ የዮሴፍ ልብስ ነው? በደም ተጨማልቆ በበረሃ ውስጥ አገኘን" ጨካኝ ወንድሞች ለያዕቆብ የሚወደው ልጁ በአውሬ እንደተበላ እንዲያምን አደረጉት። ያዕቆብ ልብሱን ቀደደ እና አለቀሰ። ማንም ሊያጽናናው የሚችል አልነበረም።
10


በግብጽ ዮሴፍ በፍርሃት እና በብቸኝነት ውስጥ ነበር። ምናልባት ወደ ቤቱ ይጓዝ ይሆናል ግን ማምለጥ አልቻለም። እርሱ በግብፃዊው በጲጥፋራ ቤት ውስጥ ባሪያ ነበር። ጲጥፋራ ዮሴፍ ምንጊዜም ጠንክሮ እንደሚሠራና ሊታመን እንደሚችል ተገነዘበ።
11


"የምትሰራው ሁሉ ወደ መልካም ይለወጣል" ጲጥፋራ አንድ ቀን ለዮሴፍ ነገረው። "እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ነው" ዋነኛ አገልጋዬ "እንድትሆን ፈልጋለሁ በጉዳዮቼ እና በአገልጋዮቼ ሁሉ ላይ አለቃ እንድትሆን ፈልጋለሁ" አለው።
12


እግዚአብሔርም በዮሴፍ ምክንያት ለጲጢፋራ መልካም ምርት እና ሀብት ሰጠው። ዮሴፍ ትልቅ ቦታ ያለው ሰው ቢሆንም አሁንም እግዚአብሔርን በታማኝነት ማገልገል ጀመረ። ይሁን እንጂ ዮሴፍ ችግር አጋጠመው።
13


የጲጥፋራ ሚስት መጥፎ ሴት ነበረች። ዮሴፍ የባሏን ቦታ እንዲወስድ ጠየቀችው። ዮሴፍ ግን ፈቃደኛ አልሆነም።
14

ጲጥፋራን በመበደል እግዚአብሔርን አልበድልም አለ። ሴቲቱ ልታስገድደው ስትሞክር ሮጦ አመለጣት። ነገር ግን ልብሱንይዛ ጨኸች።



15

“ባሪያህ ነካኝ” የጲጥፋራ ሚስት አጉረመረመች። “ተመልከት ፥ ይኸው ልብሱ” ብላ አሳየችው። ጲጥፋራ ተቆጣ። ምናልባት ሚስቱ ውሸታም መሆኗን ያውቅ ይሆናል። ነገር ግን አንድ ነገር ማድረግ ነበረበት። ታዲያ ምን ያደርግ ይሆን?



16

ጲጥፋራ ዮሴፍን እስር ቤት አስገባው። ዮሴፍ ምንም ስህተት ባይኖርበትም መራራም ሆነ ቁጡ አልነበረም። ምናልባትም ካለፉት ችግሮቹ ተምሮ ይሆናል።



17

እርሱ የትም ቦታ ቢሆንም እግዚአብሔርን ካከበረ እስር ቤት ውስጥ እንኳን ቢሆን እግዚአብሔር ደግሞ እሱን ያከብረዋል።



18

ተወዳጅ ልጅ ባሪያ ሆነ

ይህ ታሪክ የሚገኘው የእግዚአብሔር ቃል
በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ

ኦሪት ዘፍጥረት 37; ዘፍጥረት 39

“የቃልህ ፍቺ ያበራል.”
መዝሙረ ዳዊት 119:130

ክፉ ነገሮችን እንዳደረግን እግዚአብሔር ያውቃል፣ ኃጢአት ብሎም ይጠራዋል።

እግዚአብሔር እጅግ በጣም ስለወደደን አንድያ ልጁን ለመስቀል ሞት አሣልፎ በመስጠት የኃጢአትን ዋጋ በሞቱ ከፍሎልናል። ኢየሱስ ህያው ሆኖ ከሞት መነሣት ወደ ሠማይ አርጓል። አሁን እግዚአብሔር ኃጢአታችንን ይቅር ይለዋል።

ከኃጢአታችሁ ለመመለስ ከወሰናችሁ ለእግዚአብሔር እንዲህ በሉት። እግዚአብሔር አምላክ ሆይ ኢየሱስ ክርስቶስ ለእኔ ኃጢአት ሲል እንደሞተና አሁን ህያው ሆኖ እንዳለ አምናለሁ። እባክህ ወደ ህይወቴ ግባና ኃጢአቴን ሁሉ ይቅር በል ስለዚህ አዲስ ህይወት ይኖረኛል ደግሞ ከአንተ ጋር ለዘላለም እኖራለሁ። ጌታ ሆይ እንደ ልጅ ለአንተ እንድኖርልህ እርዳኝ አሜን። ዮሐ. 3.16